# እውን የትግራይ ህዝብ በሌሎች ህዝቦች ተጠልቷልን?

ክፍል አንድ

*ሀይላይ ማሙዶ* 25/04/2010 *ዓ/ም*

*በአለምም ሆነ በሀገራችን ታሪክ እንደምናውቀው አንድ ህዝብ ሌላውን ህዝብ ጠልቶ ወይም ተጣልቶ እንደማያውቅ ነው። ታድያ አሁን አሁን አንዳንድ የሀገራችን "ሙሁራን" ወይም "አዋቂዎች" ይህንን ታሪክ በሚቀይር መልኩ በአሁን ጊዜ አንድ ህዝብ ሌላውን ህዝብ እንደጠላው አስመስለው ሲናገሩና ሲፅፉ ስመለከት ለምን የሚል ጥያቄ ይጭርብኛል። ታዲያ ሳስበው የግለሰቦቹ የግል እምነትና በህዝብ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ነፀብራቅ ነው እያልኩኝ ሳልፈው ቆይቻለሁ። ይህንን አንድን ህዝብ ወይም ብሄር ኢላማ ያደረገ የጥላቻ ዘመቻ ከግለሰቦች ተነስቶ አሁን አሁን ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ሰዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ብሔሩን የመጥላትና ከዛ ብሔር የሆነ ሰው ላይ ጥቃት የመፈፀም ሁኔታ በስፋት እየተንፀባረቀ ይገኛል።*

*ይህ በአሁን ጊዜ እየተንፀባረቀ ያለውን የጥላቻ ተግባር በተለይም በአንዳንድ የአማራና ኦሮሚያ አከባቢዎች እንዲሁም በተለያዩ ዩንቨርስቲዎችና አለፍ ብሎም በስፖርት ማዘውተርያ ቦታዎች ብሔርን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች መነሻቸው በደንብ ሳያጠኑ ህዝብ ከህዝብ ወይም ብሔር ከብሔር ጋር የተደረገ ግጭት አስመስሎ በመለጠፍ ይበልጥ ግጭቱን እንዲሰፋፉ የሚያደርጉ አስተያየቶች በሀገራችን "ሙሁራን" ወይም "አዋቂዎች" የተባሉ ሰዎች በኩል ሲገለፅ ይታያል።*

*ይህን ጉዳይ በወቅቱ ተገቢው ምላሽ በተገቢው አካላት ሳይሰጥበት እየቆየ እየባሰበት መጥቷል። እኔም ፅሁፎች ሳነብና ለራሴ ተገቢውን ምላሽ እየሰጠሁ ቢሄድም እንደዚህ ሀሳቤ በፅሁፍ የገለፅኩበት ጊዜ አልነበረም። ምናልባት ያለኝን እውቀት ውስን ነው ከሚልና በዚህ ዙርያ ጥልቅ እውቀት ያላቸው ሰዎች እያሉ እንዴት ተብሎ በማለት ድፍረት በማጣት እስከ አሁን ሳልፅፍ ቆይቻለሁ። አሁን ግን ነገሮች እየገፉ ሲሄዱ፣ የአቅሜን ከሰጠሁ ሌሎች በዚህ ጉዳይ ጥልቅ ትንታኔ እንዲሰጡ መነሻ ይሆናቸዋል በማለት፣ እንዲሁም የአይጋ ፎረም አዘጋጆች የሀሳብ ብዛሀነት ለማስተናገድ ያላቸውን ቁርጠኝነት እያየሁ ሲሄድ እስቲ ይህን ፅሁፍ ጀባ ልበል በማለት ጀምሪያለሁ።*

*ውድ አንባቢዎች ይህንን ፅሁፍ ሳትንቁ ስታነቡ በተለይም ጀማሪ ከመሆኔ ጋር ተያይዞና ያለኝን እውቀት ውስን በመሆን ለሚፈጠር ክፍተት በናንተ የምትሰጡት ሀሳብ ይዳብራልና ቅሬታ እንዳይፈጥርባችሁ አደራ እላለሁ።*

*ለዚህ ፅሁፍ መነሻ የሆነኝ በሀገራችን ከሚታተሙት ጋዜጣዎችና በተከታታይ ከምከታተለው ሳምንታዊ ጋዜጣዎች አንዱ የሆነው የሪፖርተር ጋዜጣ የታህሳስ* 15/ 2010 *ዓ/ም እትም ውስጥ ስለ ሀገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ ዜጎች ምን ይላሉ በሚል ርእስ የተለያዩ ታዋቂና አዋቂ ያላቸው ሰዎች በማነጋገር ያወጣው ፅሁፍ ነው።*

*በጋዜጣው የተሰጡትን አስተያየቶች የሰዎቹ የግላቸው እምነት በመሆኑ አስተያየታቸውን አከብራለሁ። ሆኖም በሁሉም ላይ የግድ መስማማት የለብኝምና ሳልስማማም የራሴን አቋም በመያዝ ለያንዳንዱ ምላሽ መስጠት አያስፈልገኝም ብዬ ስላመንኩ አልፈዋለሁ። ይሁን እንጂ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ አንድ በጣም የተለጠጠና የጋዜጣውን አዘጋጅ እንዴት ዝም ብሎ ይፅፈዋል? በማለት ጥያቄ ያጫረብኝ ተገቢውን ምላሽ ያስፈልገዋል ብዬ ያሰብኩት የአቶ ፀጋ አስማረ የተባሉ ግለሰብ የሰጡት አስተያየት ነው።*

*አቶ ፀጋ አስማረ የነዳጅ ማመላለሻ ትራንስፖርት ባለንብረቶች ማህበር ም/ፕሬዝዳንት የሆኑት ግለሰብ በሰጡት አስተያየት በግልፅ ምንያህል በአንድ ህዝብ (የትግራይ ህዝብ) ላይ ጥላቻ እንዳላቸው በሚያሳይ መልኩ ብስለትና ሀላፊነት በጎደለው መልኩ የሰጡት አስተያየት እሳቸውን የመሰሉ ሰዎች የሚያንፀባርቁት ነውና ከተቻለ እሳቸውም ከዚህ አይነት ጥላቻ እንዲወጡ፣ ካልሆነም ከሌሎች ጋር በዚህ ጉዳይ ግልፅነት መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በማመን ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል በሚል እምነት እንድፅፍ መነሻ ሆኖኛል።*

ጋዜጣው ያላነበበ ሰው ግለሰቡ ምን ቢሉ ነው ብሎ ሊያስብ ይችላልና ለፅሁፉም መንደርደሪያ እንዲሆን በጋዜጣው ላይ የቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች ላይ አስተያየት የሰጡ በመሆናቸው የአቶ ፀጋ ምላሽ በማስቀደም የግል አመለካከቴን ለመግለፅ እሞክራለሁ።

አቶ ፀጋ እና ሌሎች ግለሰቦች የተጠየቁት አንዱ ጥያቄ በሀገራችን አሁን ያለችበትን ችግር እንዴት ልትገባ ቻለች? የሚል ነበር ከላይ እንደገለፅኩት የሌሎች ሰዎች አስተያየት እንደተጠበቀ ሆኖ አቶ ፀጋ የሰጡት ምላሽ እንደ፤-

‹‹አሁን ለተንሰራፋው ችግር መንስዔ የዘር ፖለቲካ ነው፡፡ ...አንድ ወዳጄ ተከሰሰና እሱን ለመዋስ ፖሊስ ጣቢያ ሄጄ ነበር፡፡ ዕድሜና የትምህርት ደረጃ ሁሉን ከነገርኩ በኋላ ዘርህ ምንድነው ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ኢትዮጵያዊ ነኝ አልኩት፡፡ በፍፁም ዘርህን ጥቀስ አለኝ፡፡ እኔ ከሁሉም ዘር የተነካካሁ ስለሆነ ይህ ነው ብዬ መናገር አልችልም፣ ኢትዮጵያዊ ነኝ አልኩት፡፡ ዋስ መሆን አትችልም ተባልኩ፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?.....በአንድ አገር መዓት መንግሥት ተፈጥሯል፡፡ የአንድ አገር መንግሥት አንድ ነው ሊሆን የሚገባው፡፡ አንድ መለያ ነው ሊኖር የሚገባው፡፡ የብሔሮች ስም እየተጠራ ክልል ተደራጅቶ መንግሥት መባባል በራሱ ልክ አይደለም፡፡ ....›› (መስመሩ የራሴ ነው)።

ሌላው በጋዜጣው የቀረበላቸው ጥያቄ መፍትሄው ምንመሆን አለበት? የሚል ሲሆን ህዝብን አስታኮ የሰውየው ጥላቻ የሚንፀባረቀውም እዚህ ላይ ነው። ምን አሉ የምትሉኝ እስኪ በጋዜጣው ያሉትን ላስፍረው፤-

‹‹ግልጽ ውይይት ያስፈልጋል፡፡ የትግራይ ሕዝብ ለምን በኦሮሞ ለምን በአማራ ሕዝቦች ተጠላሁ ብሎ መጠየቅ አለበት፡፡ ለውጥ ከሚፈልጉ ሕዝቦች ጎን መቆም አለበት፡፡ ከሁሉም ክልሎች የተውጣጡ የአገር ሽማግሌዎች፣ ምሁራንና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተገኙበት ግልጽ ውይይት ተደርጎ እርቅ መውረድ አለበት፡፡›› (መስመሩ የራሴ ነው)።

አቶ ፀጋ ምን ያህል በትግራይ ህዝብ ላይ ጥላቻ እንዳላቸው ከማሳየት በስተቀር የችግሩ መንስኤ ያሉትን ጉዳይ ጋር የማይገናኝ መፍትሄ ብለው ማስቀመጥ ተገቢ ሆኖ አይመስለኝም። መንስኤው የዘር ፖለቲካ ብለህ እንዴት የትግራይ ህዝብ በኦሮሞና አማራ ህዝብ ተጠላሁ ብሎ ይጠይቅ ይባላል ታዲያ? ጉዳዩ ሌላ ስለሆነ ነው እንጂ፤ እስቲ ግለሰቡ የሰጡትን አስተያየት መሰረት አድርጌ አንድ በአንድ ሀሳቤን ልግለፅ። ተከተሉኝ፤-

ይህ ፅሁፍ በሁለት ክፍል የተዘጋጀ ነው። በመጀመሪያው ክፍል በሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ አስምልክቶ በጋዜጣው የተነሳው የችግሩ መንስኤ የዘር ፖለቲካ ነው በማለት አቶ ፀጋ የሰጡት ሀሳብ የሚሞግት ሲሆን፤ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ መፍትሄው ምን እንደሆነ ተጠይቀው የሰጡትን ሀሳብ በትግራይ ህዝብ ያላቸውን ጥላቻ በህዝብ ላይ ያስታከኩበት ጉዳይ በመሆኑ ምላሽ እንደሚያስፈልገው በማመን የተዘጋጀ ነው። መልካም ንባብ፤-

## 1. በሀገራችን የዘር ፖለቲካ አለ ወይ?

አንዳንድ “ሙሁራን” ሆን ብለው ህዝቡን ለማደናገር በሚመስል መልኩ ዘርና ብሔር ቀላቅለው ሲገልፁ ስመለከት እውን ሳያውቁት ቀርተው ነው እላለሁ። በተለይም የብሔር ብሔረሰቦች በሀገራች መኖራቸውን ለማመን የሚቸገሩ አንድ ብሔር፣ አንድ እምነት፣ አንድ ቋንቋ ወዘተ የበላይነት ካልሰፈነ ሀገር አትኖርም የሚሉ እንደእነ አቶ ፀጋ ያሉ ሰዎች ለረጅም ጊዜ የሀገራችን ህዝቦች ለማንነታቸው ያደረጉትን ትግል የሚመልስ ተደርጎ የተዋቀረውን ፌደራሊዝም ስርአት ከዘር ፖለቲካ ጋር ሲያገናኙት እታዘባለሁ። በመሰረቱ ዘር(Race) እና ብሔር(Nation) ለየቅል መሆናቸውን ግልፅ ነው። ዘር ስንል ከዘረመል (DNA) ጋር የሚያያዝ እንደሆነ ብሔር ሲባል ግን ከአስተሳሰብና እምነት ጋር የተያያዘ መሆኑ ሳይገባቸው ቀርቶ አይመስለኝም።

በግልፅ በሀገራችን ህገ መንግስት ስለ ብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝቦች አስመልክቶ ያስቀመጠው ትርጓሜም ይህንን ያሳያል። በአንቀፅ 39 ቁጥር 5 እንደተገለፀው ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ህዝብ ማለት ብሎ ሲተረጉመው "ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የስነ ልቦና አንድነት ያለቸው እና በአብዛኛው የተያያዘ መልክአ ምድር የሚኖሩ ናቸው።" በማለት ያስቀምጧል። ታድያ ስለ ሰዎች ዘር የተጠየቀው የት ነው? እንዴት ቢተረጉሙት ነው ጃል?

በዚህ ህገ መንግስት ትርጓሜ አንድ ሰው ከየትም ዘር ይወለድ አባቱ ወይም እናቱ ዘራቸው ምንድነው ሳይል ብቻ ሳይሆን ብሔራቸውም የት እንደሆነ ሳይጠየቅ የራሱ ብሔር ምን እንደሆነ መግለፅ እንደሚችል ነው። በርግጥ በሀገራችን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ጉዳዩን ከዘር ጋር በማገናኘት ለጥላቻና ለግጭት ሲጠቀሙበት ስታይ ያሳዝናን። ይህንን ጉዳይ ግንዛቤ ማስጨበጥ ይችላሉ የምትላቸው የሀገራችን "ሙሁራን" ራሳቸውም በዚህ ክፍፍል ገብተው ስታይ ሀገሬ ወዴት እየተጓዝሽ ነሽ ያስብላል።

ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ለምሳሌ አንድ ሰው በአባቱ ትግራይ በእናቱ ኦሮሞ ቢሆን ያደገበት ክልል በኦሮሚያ ከሆነ እና የማህበረሰቡ ባህል፣ ልምዶች፣ ቋንቋ እና ተመሳሳይ ስነልቦና የሚጋራ ቢሆን ብሔሩ ኦሮሞ ነኝ ቢል ምን ያግደዋል? አረ ከወላጆቹ ብሔር ውጭ በሆነ ኢትዮ ሶማሊ ክልል ቢያድግና የሶማሊ ብሔር ባህል፣ ልምዶች፣ ቋንቋ እንዲሁም ተመሳሳይ ስነልቦና ይዞ ቢያድግ ብሔሩ ኢትዮ ሶማሊ ነው ቢባል ተገቢነት እንዳለው የህገ መንግስቱ ትርጉም በግልፅ ያስቀምጣል።

ይህንን ለመቀበል የሚያስቸግራቸው እንደ አቶ ፀጋ ያሉ ሰዎች የብሔር እውቅና መስጠት ሀገርን የሚበታትን አድርገው ፍርሀት በህዝቡ ለመንዛት ሲሰሩበት ቆይተዋል። አሁን ባለው ወቅታዊ ችግር በማስታከክም ፌደራሊዝሙን አፍርሶ ማንነትን ለማጥፋት አጠናክረው ቀጥለውበታል።

አቶ ፀጋ አንድ ብሔር፣ አንድ እምነት፣ አንድ ቋንቋ ...ወዘተ መኖር እንዳለበት የሚያምኑ መሆናቸው የሚያሳየውም የፌደራሊዝም ስርአቱን ለማጣጣል በአንድ ሀገር መአት መንግስታት ሆነዋል እንዲሉ አስቻላቸው። ታድያ የሳቸው ፍላጎት ድሮ እንደነበረችው በአንድ መንግስት የምትተዳደር ከላይ በቀጭን ትእዛዝ የምትነዳ ሀገርና ማንነቱን ማክበር የተነፈገ ህዝብ እንዲኖር ተመኙ። ምን ይሄ ብቻ ፍትህ በአስተርጓሚ ይሻላል ቋንቋውን ከምናስከብርለትም አሉን እንጂ ገራሚ ሰው ናቸው።

እዚህ ላይ አቶ ፀጋ ሀሳባቸው ለማጣፈጫ እንዲሆናቸው ድሮ ሲተረት የነበረውን ሀሳብ እንደ አዲስ ምሳሌ ብለው ያቀረቡት ጉደይ አለ። እሱም ዋስ ለመሆን ብለው ሲሄዱ ዘር በመጠየቃቸው መናገር ስላልፈለጉ ግን ዋስ መሆን አትችልም ተብለው እንደተመለሱ የገለፁት ነው። ይገርማል ለካ አንዳንዱ ሰው እድሉ ስላገኘ ብቻ የመጣለትን ነው የሚያወራው።

እኔ የገረመኝ ግን ጋዜጠኛው እንዲህ ሲሉት የት? እንዴት? ለምን? ብሎ አንድ እርምጃ እንኳን መጠየቅ ሳይፈልግ እንደወረደ መፃፉ ነው። ወይስ ጋዜጠኛውም ዋስ ለመሆን ዘር እንደሚጠየቅ ያምናል? ለነገሩ አሁን አሁን ጋዜጣው ወቅታዊ ሁኔታውን አስመልክቶ የሚያወጣቸው ፅሁፎች ግራ እያጋቡኝ ስለሆነ ወዴት እየሄደ ነው እንድል አስገድዶኛል።

ስለ ጋዜጣው አስመልክቶ አንድ ምሳሌ ልግለፅና ወደ ጉዳዩ ልመለስ በአሁን ወቅት በሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎች እየታዩ ያሉ ብሔርን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች መነሻው አዲግራት ዩኒቨርሲቲ እንደሆነ በተደጋጋሚ ሲገልፅ ሳይ ወዴት? ወዴት? እላለሁ። መቱና ጅማ ዩኒቨርሲቲዎች የነበሩ የአንድ ብሔር ተማሪዎች ጉዳት ሲደርስባቸው ተሰደው ጋምቤላ ክልል የተጠለሉት፣ እንዲሁም በውይይት ወደ ዩኒቨርሲቲው ሲመለሱ መኪናቸው ላይ ድንጋይ የተወረወረባቸው ከአዲግራት ዩኒቨርሲቲ ግጭት በፊት አይደለም እንዴ? አረ ለመሆኑ የስፖርት ክለባቸው ለመደገፍ ብለው ወልድያ

የተጓዙት ወጣቶች በብሔራቸው ምክንያት ያ ሁሉ ችግር ሲደርስባቸው የነበረው ከአዲግራት ዩኒቨርሲቲ ግጭት በኋላ ይሆን እንዴ? በማለት የጊዜ ሑደት ለውጥ ካለ እንድጠይቅ አድርጎኛል።

በእርግጥ የአዲግራት ዩኒቨርሲቲው ግጭት በመሰረቱ የምቃወመውና ተገቢ ያልሆነ ግጭት እንደሆነ አምናለሁ። ግን ለምን እንደ መንስኤ እንዲደጋገምና ተገደን እንድናም ይደረጋል? ከዛ በፊት የተደረጉ ግጮች መንስኤ መሆን አቃታቸው ወይ? ለማለት ነው። ለማንኛውም በዚህ ጉዳይ ፈጣሪ ከፈቀደ የምመለስበት ስለሆነ እዚህ ላቁመውና ወደ የዛሬ ርእሰ ጉዳይ የሆነው የአቶ ፀጋ እና የሳቸው ሀሳብ የሚጋሩ ሰዎች ልመለስ።

በሀገራችን ላይ አንድ ሰው ዋስ ለመሆን ፈልጎ ከየት ዘር እንደሆነ የሚጠየቅበት የህግ አግባብ የለም ብቻ ሳይሆን አሁን ባለው የፌደራል ስርአት መቼም ቢሆን የሚጠየቅበት አግባብ አይኖርም። እንዲህ በግልፅ ዘራቸው ተጠይቀው ከሆነም ተገቢነት እንደሌለው ጠያቂውን የመሞገትና መብታቸው የማስከበር ሙሉ መብት ደግሞ አቶ ፀጋ አላቸው። መቼስ የብዙ ተሽከርካሪዎች ባለንብረት እንዲሁም የማህበራቸው መብት ለማስከበር በሀላፊነት የተመረጡ ሰው ሆነው ይህንን መብት ማስከበር ያቅታቸዋል ለማለት ይከብደኛል።

ግን እስቲ ቀለል እናድርገውና ሰውዬው የብሔሮች መብት ከዘር ፖለቲካ ጋር የሚቀላቅሉ ስለሆነ የተጠየቁት ብሔራቸው ይሆናል እንበል። ታድያ አቶ ፀጋ እስከ አሁን ብሔራቸው እንዴት ሳያውቁ ቆዩ? መቼስ ከመገረም በስተቀር ምን ይባላል? ሰውዬው በዚች ሀገር እየኖሩ የቀበሌ መታወቅያ የላቸውም እንዴ? አረ ይኖራቸዋል። ታድያ ብሔራቸው ምን ብለው አፃፉ? ባያምኑበትም ብሔራቸው ሳያፅፉ መታወቅያ አይወስዱም። ስለሆነም ዋስ ለመሆን የሄዱበት ቦታ ያለው ጠያቂ ሰውዬ መታወቂያቸው በማየት ብሔራቸው መሙላት አይችልም እንዴ? እነዚህን የመሰሉ ቀላል ጥያቄዎች በማንሳት አቶ ፀጋ የውሸት ምሳሌ ማቅረባቸው ማወቅ ይቻላል።

እግረ መንገዴ በአይጋ ፎረም ድህረገፅ በተደጋጋሚ ሀሳቡን በነፃነት የሚገልፀው ሲሳይ መንግስቴ የተባለ ግለሰብ ስለ የቀበሌ መታወቅያ ላይ ብሔርን መግለፅ አስፈላጊነትና ህጋዊነት አስመልክቶ ያሰፈረው ፅሁፍ የምጋራውና የማልጋራው ሀሳብ እንዳለበት እየገለፅኩ። በዚህ ጉዳይ በሌላ ጊዜ የምመለስበት ሆኖ አሁን ባለው ሁኔታ ግን በመታወቂያችን ላይ ብሔር ማፃፍ የግድ እንደሚል የሚያሳየን ነው።

ታድያ ከዚህ በመነሳት አቶ ፀጋ ወይም መታወቂያ የላቸውም፤ አልያም ፎርጂድ ነው ያሰሩት፤ ህጋዊ ከሆነ ደግሞ ብሔራቸው አስፍረዋል/አፅፈዋል። በመታወቂያቸው ያለውን ብሔራቸው ለመናገር ለምን አልፈለጉም? ብለን ብንጠይቅ ደግሞ ትንሽ በየዋህነት ካየነው ሰውዬው ዋስ መሆን ስላልፈለጉ ማምለጫ ዘዴ ተጠቀሙባት እንላለን። አይይ በደንብ ይፈተሽ ከተባለ ግን የብሔር ማንነት መከበር ስለማይዋጥላቸውና በብሔር ጥላቻ ስለተዘፈቁ እንደሆኑ ያስረዳናል።

ሲጠቃለል አቶ ፀጋ ሆን ብለው ያላቸው የብሔር ጥላቻ ለመግለፅ በሀገራችን ያለው ማንነትን መሰረት ያደረገው ፌደራሊዝም ስርአት ለማጥላላት አጋጣሚውን ተጠቅመው የሌለውን የዘር ፖለቲካ አለ ብለው የችግሩ መንስኤ በማለት ገልፀውታል። እንደዚህ ያሉ ሀሳቦች ደግሞ በወቅቱ በሀሳብ ካልተመቱ ወጣቱን ሀይል በተሳሳተ መንገድ በማነሳሳት የብሄር ማንነት ከዘር ጋር በማያያዝ አብሮት የኖረና የተዋለደ ህዝብ ላይ እንዲጨክን ያደርገዋል።

በተለይም ብሔርና ዘር ለይቶ ካላየና ብሔር ማለት ከአስተሳሰብና እምነት ጋር የሚያያዝ መሆኑን ካልተረዳ የማን ልጅ ነው እያለ በመከፋፈል ወንድም/እህት ከወንድም/ ከእህት ጋር የሚጨካከኑበት ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጓል። ይህ ደግሞ አንዳንድ የሀገራችን “ሙሁራን” ሆን ብለው ለረጅም ጊዜ የሰሩበትና በወቅቱ ተመጣጣኝ የሆነ ምላሽ ያልተሰጠበት፤ ይበልጥም እየሞቀን ስናባብሰው የነበረ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ካልሆነ በስተቀር አሁን ያለው የፌደራሊዝም ስርአት የዘር ፖለቲካ አይደለም ብቻ ሳይሆን መቼም ቢሆን የግጭት መንስኤ ሊሆን አይችልም። እዚህ ላይ ግልፅ መሆን ያለበት

ይበልጥ የፌደራል ስርአቱን ለማጠናከር መሻሻል ወይም መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች እንዳሉ እንደተጠበቀ መሆኑ ነው።

**ክፍል ሁለት ይቀጥላል.....**